ጳጳሳዊ ማህበራት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ዲሬክተር የ**2011** ዓ.ም የተልዕኮ እሁድን አስመልክቶ ያስተላለፉት መልዕክት

**PMS IN ETHIOPIA NATIONAL DIRECTOR MESSAGE FOR 2018 WORL MISSION SUNDAY CELEBRATION**

ብፁዓን ጳጳሳት፣ ክቡራን ካህናት፣ ገዳማዊያንና ገዳማዊያት፣ የተወደዳችሁ የእግዚአብሔር ሕዝብ ምዕመናንና ምዕመናት ሁላችሁ፤-

ከሁሉ በማስቀድም ‹‹ከአባታችን ከእግዚአብሔርና ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን” (1ቆሮ 1፡3-4) በማለት መልካሙን ሁሉ እመኝላችኋለሁ።
ከዚህ በመቀጠል በእየዓመቱ የሚከበረውን ዓለም አቀፍ የተልዕኮ ቀን እንደ ሐዋርያው ጳውሎስ “ወንጌል ባልሰብክ ወዮልኝ” (1ቆሮ 9፡16) ካላችሁ ወንጌልን የመስበክ ጉጉት በመነሳሳት፣ባደረገችሁት የዘወትር ጸሎታችሁና በፍቅር የተሞላ ልግስናችሁ “እግዚአብሔር በደስታ የሚሰጠውን ይወዳልና እያንዳንዱ በልቡ እንዳሰበ ይስጥ በኀዘን ወይም በግድ አይደለም” (2ቆሮ 9፡ 7) ምክንያት የተነሳ ለ2010 ዓ. ም (2017 እ.ኤ.አ) ዓለማቀፍ የተልዕኮ ቀን በደማቅ መንፈሳዊንትና ከ **477,000.00** ብር **(**አራት መቶ ስባ ሰባት ሺሳ ብር) በላይ የምሕረት፣የእርቅ፣የፍቅርና የሰላም ወንጌል እንዲስፋፋ ላደረጋችሁት አስተዋጽኦ ከፍ ያለ መስጋናዬን በማቅረብ እግዚአብሔር ይባርካችሁ እላለሁ። በዚህ አጋጣሚ የካቶሊክ ሐዋርያዊ ተልዕኮ ቅስቀሳ ቡድን በኢትዮጵያን ላደረጉት ከፍተኛ የፍቅር አገልግሎት፣ የተልዕኮና የጥሪ ምንነት አስተምህሮና ውጤታማ ቅስቀሳ ከልብ አመሰግናለሁ።

እንደሚታወቀው የካቶሊክዊት ቤተክርስቲያን ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰጣትን ተልዕኮ ባላደራነት ለመወጣት በሁሉም መስክ ያላሰለሰ ጥረት በማድረግ ላይ ትገኛለች። ምክንያቱም የወንጌል ተልዕኮ ገና በጅምር ላይ ነው። ዓለም የኢየሱስ ክርሶቶስን ወንጌል በጽኑ ትፈልጋለች። ሁሉም የሰው ልጆችና ማህበረሰቦች ለእያንዳንዱ ሰው ስጦታ የሆነውን የእግዚአብሔርን የመዳን መልዕክት የመስማት መብት አላቸው። ይህም በጣም አስፈላጊ ሆኖ የምናገኘው አሁን ባለንበት ጊዜ ኢ-ፍታሐዊነት፣ ጦርነቶችና የሰዎች ልጆች ስቃይ መፍትሔ የሚሻ በመሆኑ ነው። የምህረትና የይቅር ባይነት ወንጌል በሰዎች ዘንድ ደስታን፣ እርቅን፣ ፍትሕንና ሠላምን ያመጣሉ። የወንጌል ተልዕኮ ‹‹ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ፤ በአብ፣ በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቋኋቸው፤ እኔ ያዘዝኳችሁን እንዲተገብሩም አስተምሯቸው (መቴ 28፡19-20) የሚለው መልዕክት በከንቱ አይደለም፤ ይልቁንም ይህ ትዕዛዝ ሁላችንም ታዛዥ እንድሆን አጠናክረን እንድቀጥልና ለያይቶን የነበረውን የጥል ግድግዳ የሚየፈርስና አንድ የሚያደርግ ሰላማችን ኢየሱሰ ክርስቶስ መሆኑን (ኤፌ 2፡13-14) እንድናውጅ ይጋብዘናል (ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ፍራንቼስኮስ፤ እ.ኤ.አ.*2017* ዓለም ዓቀፍ የተልዕኮ ቀን መልእክት ይምልከቱ)።

ይህ የባላደራነት ተዕልዕኮ ቃለ እግዚአብሔርን በማወጅ፤ ስርዓተ-አምልኮን በመፈፀም በተለይም ምስጢራትን በማደልና የፍቅር ግልጋሎትን መስጠት የማይነጣጠል ጥልቅ የሕልውና ሀላፊነተዋ ነው (ር.ዕ ሊ.ጳጳሳት ቤኔዲክቶስ 16ኛ፣ እግዚአብሔር ፍቅር ነው ቁ.25፣ ይመልከቱ)። የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያንም ይህን ተልዕኮ በመላው የሀገሪቱ ክፍሎች የሰዎችን ሁለነተናዊ ዕድገት ማዕከል በማድረግ በአስራ-ሦስት ሀገረ-ስብከቶች በመዋቀር በማከናወን ላይ ትገኛለች። መንፈሳዊና ቁሳዊ ድጋፍ በማድረግ በዓለም ከሚገኙ የካቶሊክ ቤተክርስቲያን አባላት ሁሉ ጋር ሕበረቷንና አንድነቷን ትገልጻለች።

ምክንያቱም ስብከተ-ወንጌል የሁሉንም ተሳተፎና የተቀናጀ አካሄድን፤ ለወንጌል አገልግሎት መመሰጠተን፤የእግዚአብሔርን ፍቅር ለሌሎች ለማካፈል የእምነት ቁረጠኝነትን፤ ለወንጌል ምስክርነት በቃልም ሆነ በሕይወት ፈቃደኛ መሆንን የሚጠይቅ ነው። በቅድስት መንበር የእምነት ስርጭት ማኅበር ኃላፊነት ስር የሚተዳደር ጳጳሳዊ ልዑካን ማኅበራት ማለትም፡-

ጳጳሳዊ ማህበራት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ዲሬክተር የ**2011** ዓ.ም የተልዕኮ እሁድን አስመልክቶ ያስተላለፉት መልዕክት

**PMS IN ETHIOPIA NATIONAL DIRECTOR MESSAGE FOR 2018 WORL MISSION SUNDAY CELEBRATION**

1) የእምነት ስርጭት ማኅበር በዋናነት የወንጌል ልዑካን ስራዎችን በመንፈሳዊና ቁሳዊ ድጋፍ የሚየደርግና ምዕመናን ሁሉ በስብከተ-ወንጌል ተሳትፎ እንዲየደርጉ የሚያበረታታና ዕድል የሚሰጥ፣
2) የሕጻናት/ታዳጊዎች ልዑካን ማሕበር (የሕጻኑ ኢየሱስ)፡-ሕጻናት/ታዳጊዎች በጸሎት፤በልዑካዊነት መንፈስ፤በጥሩ ክርስቲያናዊ እሴቶች ተኮትኩተው እንዲያድጉ መንፈሳዊና ቁሳዊ ድጋፍ የሚሰጥ፣
3) የሐዋርየው ቀዱስ ጴጥሮስ ልዑካን ማሕበር፤ አገር በቀል ካሕናትን፤ልዑካንን፤ገዳማዊያንንና ገዳማዊያትን ለማነፅ መንፈሳዊና ቁሳዊ ድጋፍ ድጋፍ የሚየደርግ፣
4) የልዑካን ሕብረት፡- የዘርዓ-ካሕናት ተማሪዎች፣ አገር በቀል ካሕናትን፣ገዳማዊያንና ገዳማዊያትንና ምዕመናን ትጉህ ልዑካን ይሆኑ በጸሎትና በመስዕዋት አማካይነት ማስተማር፤

የበተክርስቲያን ተልዕኮ ዕውን ለማድገ በተቀናጅ መልኩ ያከናውናሉ።

በጥቅሉ ጳጳሳዊ ልዑካን ማኅበራት ሁሉም የክርስቲያን ማህበረሰቦች ከሚኖሩበት ሥፍራና ከምቹ ጓዳዎቻቸው ወጥተው ለሁሉም ወንጌል መስበክ እንዲችሉ ለማነሳሳት እንቁ እድል ይፈጥራሉ።

ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ፍራንቼስኮስ የ2011 ዓ.ም (2018 እ.ኤ.አ) ዓለም ዓቀፍ የተልዕኮ ቀንን ከወጣቶች ጋር አንድ ላይ ሆነን ወንጌልን ለሁሉም እናድረስ በሚል መሪ ቃል እንድናከብር በመልዕክታቸው ጋብዘውናል። ምክንያቱም እርሳቸው እንደሚሉትና እኔም እነደማምነው  ወጣቶች የተልዕኮ ተስፋዎች ናቸው። ኢየሱስ ክርስቶስና እርሱ የሰበከው መልካም ዜና ዛሬም ብዙ ወጣቶችን እየሳበ ነው። ወጣቶች ሰብዓዊነትን በብርታትና በጋለ ሥሜት ማገልገል የሚችሉበትን መንገድ ማግኘት ይፈልጋሉ። ‹‹የዚህ ዓለም ክፋት ሳይበግራቸው በተለያዩ በጎ ሥራዎችና ተግባራት ውስጥ የሚሳተፉ ብዙ ወጣቶች አሉ … ወጣቶች ‹የመንገድ ላይ ሰባኪዎች› ሆነው በደስታ ኢየሱስን ወደ ሁሉም መንገዶች፣ የከተማ አደባባዮች እና ወደ የዓለም ክፍሎች ሲያመጡ ማየት ምንኛ ውብ ነው (የወንጌል ደስታ፣ 106)። ወጣትነት የእግዚአብሔር ስጦታ ነው።  ወጣቶች ጥራት ያለው ትምህርት እጦት፣የድህነት፣የስራ አጥነት፣የስደት፣የፖለቲካ ብዝበዛና የተለያዩ ሱሶች መጠመድ ሰለባዎችና ትክክለኛና ሚዛናዊ የሆነ የሕይወት ምርጫ ማድረግ እክል ምክንያቶ ተስፋ ሊቆረጡ ስለሚችሉ “ከእነርሱ ጋር የሚጓዙ ወንጌልን እንዲወዱና በተለይ ከአቻዎቻቸው ጋር እንድካፈሉ ብሎም እውነትኛ ታማኝ መልዕክተኞች እንዲሆኑ የሚያስተምአቸው መስካሪዎችና አስተማሪዎች ያስፈልጉአቸዋል”(ር.ዕ ሊ.ጳጳሳት ቤኔዲክቶስ 16ኛ፣የአፍሪካ ታማኝነት፤§ 61)። በተለይም እ.አ.አ በ2018 ዓ.ም. የሚካሄደው የጳጳሳት ሲኖዶስ ‹‹ወጣቶች፣ እምነትና የጥሪ ሚዛናዊ አስተውሎት›› በተሰኘ መርዕ-ሐሳብ ሥር ወጣቶች  የፈጠራና የሐሳብ ችሎታቸውን የሚፈልግ የጋራ ተልዕኮ ኃላፊነት አካል እንዲሆኑ እድል ይሰጣል ተብሎ ይታመንበታል።

የምሕረት፣የእርቅ፣የፍቅርና የሰላም ወንጌልን በቃልም ሆነ በሕይወት የአገልግሎት ምስክርነት መስጠት እንድችሉ ጥሩ ስነምግባርን በማስተማር፣ በክርስቲያናዊ እሴቶችና አስተምህሮዎች በአግባቡ በመቅረፅ በማሰልጠን ወጣቶችን  በበምናቀደው የተለያዩ የሐዋርየዊ ስራዎች በብቃት ማሳተፍ ቤተክርሰቲያን ከክርሰቶስ የተቀበለችውን ተልዕኮ አውን ማድረግ የስቸላታል የሚል እምነት አለኝ።  በዚሁ መሰረት ወጣቶች ሊወደዱ፣ ሊከበሩ፣ ሊመሰገኑና ስጦታቸውን ለእግዚአብሔር መንግስት ማስፋፋትና ለቤተክርስቲያን እድገት ሊያውሉት እንዲችሉ ጳጳሳዊ ልዑካን ማኅበራት በኢትዮጵያ የበኩሉን ድርሻ ለመወጣት ጥረት እነደሚያደርግ ለመግለጽ እወዳለሁ።

ጳጳሳዊ ማህበራት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ዲሬክተር የ**2011** ዓ.ም የተልዕኮ እሁድን አስመልክቶ ያስተላለፉት መልዕክት

**PMS IN ETHIOPIA NATIONAL DIRECTOR MESSAGE FOR 2018 WORL MISSION SUNDAY CELEBRATION**

ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ፍራንቼስኮስ እ.ኤ.አ.ጥቅምት የ2019 ዓ.ም (ጥቅምት 2012 ዓ.ም) በመላው የካቶሊክ ቤተክርስቲየን ልዩ የተልዕኮ ወር እንዲሆን ስላወጁ፤ እኛም የኢትዮጵያ ካቶሊከ ቤተክርስቲያን አባላት ሁላችን ስለቤተክረስቲያናችን ተልዕኮ ይበልጥ እነድናሰላስል፤ ስለስብከተ-ወንጌል ስርጭት ምን መደረግ እነደለበት በመወያየት የመፍትሄ ሀሳቦችን በማቀረብና በመሳትፍ፤ ለቤተክርስቲያናችን፣ እምነታችንን ለማስፋፋት በተጠናከረ መልኩ እንድንችል በመጸለይ እንደዚሁም “የምድር ጨውና የዓለም ብርሃን” (ማቴ 5፡13-14) የሚቻለንን ሁሉ እንድናደርግ በቅድሚያ ጥሪዬን አቀርባለሁ።

በመጨረሻም በጥቅምት 11 ቀን 2011 ዓ.ም ዓለም አቀፍ ቀን ስናከብር፡- ለአገራችንና ለዓለማችን ሰላም በመጸለይ፤ የምሕረት፣የእርቅ፣የፍቅርና የሰላም ወንጌልን በቃልም ሆነ በሕይወት የአገልግሎት ምስክርነት በመስጠት፤ ይህ ወንጌልም በዓለሁሉ ይስፋፋ ዘንድ እግዚአብሔር ከሰጣቸሁ ፀጋና በረከት ሁሉ መንፈሳዊና ቀሳዊ ድጋፍ ታደርጉ ዘንድ በትሕትና በእግዚአብሔር ስም እጠይቃለሁ።
የእግዚአብሔር መንግስት ይስፋ! እግዚአብሔር ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿንም ይበርክ!

## የቫቲካን የስብከተ ወንጌል ዋና ጽ/ቤት ጳጳሳዊ ልዑካን ማኅበራት

## የተጠመቀችና የተላከች - በዓለም ውስጥ በተልዕኮ የተሰማራች የክርስቶስ ቤተክርስቲያን ልዩ የልዑካን ወር፣ እ.አ.አ ጥቅምት 2019

### እ.አ.አ ጥቅምት 2019፣ ልዩ የልዑካን ወር

እ.አ.አ በጥቅምት 2017 በዓለም አቀፍ የተልዕኮ ቀን በብስራተ ገብርኤል (አንጀሉስ) የጸሎት ጊዜ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ፍራንቼስኮስ የፈርንጆቹ 2019 ዓ.ም. ጥቅምት ወርን ልዩ የተልዕኮ ወር ብለው የመሰየም ሐሳብ እንዳላቸው ይፋ አደረጉ:: ምክንያቱም ይህ ቀን በርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ቤኔዲክት 15ኛ በስብከተ ወንጌል መስፋፋት ላይ የተጻፈ ማክሲሙም ኢሉድ (Maximum Illud) የተሰኘ ሐዋርያዊ ደብዳቤ 100 ዓመት ክብረ በዓል ጋር አንድ ቀን ላይ ስለሚውል ነው:: በተመሳሳይ ቀን ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ለቫቲካን የስብከተ ወንጌል ዋና ጽ/ቤት (CEP) ሀላፊ እና የጳጳሳዊ ልዑካን ማኅበራት (Pontifical Mission Societies – PMS) ጠቅላይ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ካርዲናል ፈርናንዶ ፊሎኒ አንድ ደብዳቤ ጻፉ:: በዚህ ደብዳቤ አማካይነት ክብረ በዓሉን እንዲያስናዱ ፣ ይህንም

የወንጌል ስርጭት ልዑካን ማኅበር በክብርት ፖሊን ማሪ ጃሪኮ እ.አ.አ በ1822 በሊዮን ፈረንሳይ አገር የተቋቋመ ሲሆን ምእመናን ቁሳዊ ድጋፍ እንዲያደርጉ በማበረታታትና ለ«ተልዕኮ ለሁሉም ህዝብ» (missio ad gentes) በመስጠት የሚሰሩ ሰዎችን ጌታ እንዲጠራቸው በመለመን በምእመናን ዘንድ ጸሎትና ራስን መስጠት እንዲጠነከር እያደረገ ነው::

የቅዱሳን ሕጻናት ማኅበር በፈረንሳይ አገር ፓሪስ ከተማ እ.አ.አ በ1843 በናንሲ ሀገረ ስብከት ጳጳስ ብጹዕ ቻርልስ አገስት ዴ ፎርቢን-ያንሰን በይፋ ተቋቋመ:: በዓለም የሚገኙ ልጆች በእምነትና በጸሎት የፍቅር ሥራና «ልጆችን ልጆች ያግዛሉ» የሚል መፈክር አንግቦ ልጆች ያላቸውን ከሌሎች ጋር መጋራት እንዲችሉ ይረዳል::

የሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ማኅበር የተቋቋመው በጂን እና ስቴፋኒ ቢጋርድ በፈርንሳይ አገር በኬይን ሲሆን ዓላማውም በጸሎት መሥዋዕትና በቁሳዊ ድጋፍ የተልዕኮ ትብብርን ማጠናከርና ማስተባበር ነው፤ ይሄውም ቤተክርስቲያን በአዲስ መልክ እየተስፋፋች ባለችባቸው የተልዕኮ አገራት ወደ ፊት ካህናትና ገዳማውያን መሆን የሚፈልጉ ሰዎችንና አስተማሪዎቻቸውን በትምህርት ማነጽ ነው::

የልዑካን ኅብረት የጳጳሳዊ የተልዕኮ ተቋም (Pontifical Institute for Foreign Missions) ልዑክ ካህን በሆኑት በብጹዕ ፓውሎ መና መንፈስ አነሳሽነት እ.አ.አ በ1916 በርዕሰ ሊቃ ጳጳሳት ቤኔዲክት 15ኛ ይሁንታ አገኘ:: የሦስቱ የተልዕኮ ማኅበራት አንኳር ነው ተብሎ የሚወሰደው ይህ ማኅበር ዓላማው በቤተክርስቲያን ውስጥ የልዑክነትን ልባዊ ፍላጎት መቀስቀስ፣ ለልዑካን የትምህርት ህንጸት አስተዋጽኦ ማድረግና በክርስቲያናዊ ማኅበራት ዘንድ ለተልዕኮ የጋለ ፍላጎት እንዲቀሰቀስ ማስቻል ነው::

በተጨማሪ የስብከተ ወንጌል እንቅስቃሴ የጸሎት አካልና ተጨባጭ ክፍል መሆን ይፈልጋል::

### እ.አ.አ 2022፣ የቤተክርስቲያን ተልዕኮ ኢዮቤሊዩ

እ.አ.አ በ2022 የተለያዩ አስፈላጊ ክስተቶች ይከናወናሉ፤ የቫቲካን የስብከተ ወንጌል ዋና ጽ/ቤት (CEP) ከተቋቋመ 400ኛ ዓመቱን ያከብራል:: የወንጌል ስርጭት ልዑካን ማኅበር (Missionary Society for the Propagation of the Faith) ከተቋቋመ 200ኛ ዓመት ይሞላዋል:: የመጀመሪያዎቹ የተልዕኮ ማኅበራት ማለትም ጳጳሳዊ የወንጌል ስርጭት ልዑካን ማኅበር፣ ጳጳሳዊ የሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ማኅበር እና ጳጳሳዊ የቅዱሳን ሕጻናት ማኅበር ጳጳሳዊና ዓለም አቀፋዊ ማንነታቸውን ከተቀበሉ 100 ዓመታት ተቆጥረዋል:: እነዚህ የኢዮቤልዮ ክብረ በዓላት ምናልባት ለቤተክርስቲያን በጥምቀት የተቀበለችውን የልዑክነት ሥራ ግንዛቤዋን ሕያውና ብቁ አድርጋ እንድትጠብቅ ሌላ እድል የሚሰጣት አጋጣሚ ይሆናል:: የተልዕኮ ችግር የእምነት ችግር ከሆነ፣ የቤተክርስቲያን እምነት ብሱልነት የሚገለጸው ሁሉንም ሰውና ነገር ወደ ክርስቶስ በመሳብ ነው:: ከፊታችን እየቀረበ ያለው ልዩ የልዑካን ወር ምናልባት የእምነት፣ የጸሎት፣ የአስተንትኖና የፍቅር ሥራ ደፋር ጉዞ ጅማሬ ነው:: ይህ ጉዞ በጥቅምት 2019 የሚያልቅ አይደለም፣ ነገር ግን «ለሁሉም ህዝቦች» ወንጌልን ማድረስ የሚለው ሐሳብ የመላው ቤተክርስቲያን ሕይወትና ተልዕኮአዊ ተፈጥሮ ሞተርና ዋና መሪ ሐሳብ እንዲሆን በተለያየ መልክ ቁርጥ ውሳኔ የሚደረግበት ወር ነው::

ትርጉም:- ጳጳሳዊ ልዑካን ማኅበራት በኢትዮጵያ

ሲያደርጉ ስለዝግጅቱ በሚመለከታቸው ቤተክርስቲያናት ዘንድ፣ በገዳማውያን እና ገዳማውያት ተቋማትና የሐዋርያዊ ሥራዎች ማኅበራት (Institutes of Consecrated Life and Societies of Apostolic Life) እንዲሁም ቤተክርስቲያን ውስጥ ባሉ ማኅበራት፣ እንቅስቃሴዎችና ሌሎችም አደረጃጀቶች ዘንድ ግንዛቤ የመፍጠር ኃላፊነት ተሰጣቸው::

የቤተክርስቲያንን ተልዕኮ በተመለከተ የህዝበ እግዚአብሔርን ጥምቀት ግንዛቤ ለመቀስቀስ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ፍራንቼስኮስ ለልዩ የልዑካን ወር የሚከተለውን መርሕ ሐሳብ አቅርበዋል፣ «የተጠመቀችና የተላከች - በዓለም ውስጥ በተልዕኮ የተሰማራች የክርስቶስ ቤተክርስቲያን»:: በእርግጥ የ «ተልዕኮ ለሁሉም ህዝብ» (missio ad gentes) ግንዛቤን መልሶ መቀስቀስና ወንጌልን በአዲስና በጋለ ስሜት የመስበክ ወኔን ማሳደስ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ቤኔዲክት 15ኛ በማክሲሙም ኢሉድ (Maximum Illud) ስለ ሐዋርያዊ ትኩረት የጻፉትንና ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ፍራንቼስኮስ በኢቫንጄሊ ጓዲየም (የወንጌል ደስታ) ውስጥ የገለጹትን የሐዋርያዊ ሕያውነትን ሐሳብ አንድ ላይ የሚያጠቃልሉ መርሕ ሐሳቦች ናቸው:: «ተልዕኮአዊ አስተሳሰብ እና ተግባር የሁሉም የቤተክርስቲያን ሥራ ዓይነተኛ ጸባይ መሆን አለበት (የወንጌል ደስታ 15)::» «ይህ ደግሞ የኢየሱስን ተልዕኮ የቤተክርስቲያን ማዕከል በማድረግ፣ የመዋቅርዎቿ ብቃት፣ የጥረቷን ውጤት፣ የአገልጋዮቿን ፍሬያማነትና አገልጋዮቿ የሚፈጥሩት ደስታ መስፈርት እንዲሆን ማድረግ ማለት ነው:: ምክንያቱም ያለ ደስታ ማንንም ወደ እኛ መሳብ አንችልም:: (ከላቲን አሜሪካ ጳጳሳት ጉባዔዎች ኅብረት (CELAM) ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ጋር የተደረገ ስብሰባ፣ ቦጎታ፣ እ.ኢ.አ መስከረም 2017)::»

ወደ ተሰቀለው፣ ከሞት ወደ ተነሳውና ሕያው ወደ ሆነው ኢየሱስ እንደ ግለሰብም ሆነ እንደ ማኅበር በሚኖረን መለወጥ፣ ቃሉን በመስበክና በክርስቲያናዊ አኗኗር ለወንጌል ህይወትና ለፋሲካ ደስታ (ሉቃ 24 ፣ 46-49) ያለንን ኃይልና የጋለ ስሜት ያድስልናል::

ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ባሉት መሠረት ለልዩ የልዑካን ወር ክብረ በዓል ዝግጅት ጉዞ በጥልቀት እንዲሰማን አራት አቅጣጫዎች ተቀምጠዋል፤

1. በቤተክርስቲያን ውስጥ ሕያው ሆኖ ካለው ከኢየሱስ ጋር በግል መገናኘት፣ ይህም በቅዱስ ቁርባን ውስጥ፣ በእግዚአብሔር ቃል፣ እንዲሁም በግልና በጋራ ጸሎት ውስጥ ነው::
2. ምስክርነት፣ የተልዕኮ ቅዱሳን፣ ሰማዕታትና ሌሎች የኃይማኖት አባቶች በዓለም ላይ በየስፍራው ለምትገኝ ቤተክርስቲያን መገለጫ ናቸው::
3. የተልዕኮ ሕንጸት፣ የመጽሐፍ ቅዱስ፣ የትምህርተ ክርስቶስ፣ መንፈሳዊና ሥነመለኮታዊ
4. የተልዕኮ የፍቅር ሥራ

## የወንጌል ስርጭት ጽ/ቤት (ፕሮፖጋንዳ ፊዴ) እና የጳጳሳዊ ልዑካን ማኅበራት

በአንድ ሰሞን የወንጌል ስርጭት ጽ/ቤት (ፕሮፖጋንዳ ፊዴ) ተብሎ ይታወቅ የነበረ የቅድስት መንበር የተልዕኮ ጽ/ቤት (The Missionary Dicastery of the Holy See) የተቋቋመው እ.ኢ.አ. በ1622 በርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ግሬጎሪ 15ኛ ሲሆን ዓላማውም የቤተክርስቲያንን የስብከተ ወንጌልና የተልዕኮ ትብብር ሥራን ለማበረታታት፣ ለማቀናጀትና ለመምራት ተቋቋመ:: እ.ኢ.አ በ1967 ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ጳውሎስ 6ኛ የዚህን ጽ/ቤት ሐዋርያዊ

አገልግሎት አስፈላጊነት ለማጠናከር፣ ክፍሉን የስብከተ ወንጌል ዋና ጽ/ቤት (CEP) ብለው ሰየሙ:: ቀጣይነት ባለው የፍቅር ሥራ የሚገለጥ የክርስትና እምነት ተጨባጭ ፍሬያማነት፣ እያንዳንዱ ምስጢረ ጥምቀት የተቀበለ ክርስቲያን የዓለም አቀፍ ቤተክርስቲያን እረኛ የሆኑትን የርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳትን ተልዕኮ የመደገፍና የመርዳት ኃላፊነት አለበት:: ጸሎት፣ ራስን መስጠት፣ የልዑክነት ጥሪ፣ ቁሳዊ ድጋፍ ዛሬም ለዘመናት የቆየውን የጳጳሳዊ ልዑካን ማኅበራት ቁርጠኝነትን ያስቀጥላሉ:: የጳጳሳዊ ልዑካን ማኅበራት በ19ኛና 20ኛ ክፍለ ዘመን ውስጥ ለምእመናንና ገዳማውያን ተልዕኮ ከነበረው ጥልቅ መቆርቆር የተፈጠረ ነው:: «የቫቲካን የስብከተ ወንጌል ዋና ጽ/ቤት (CEP) እና የጳጳሳዊ ልዑካን ማኅበራት አንድ ላይ በመሆን ከተልዕኮና ከሚያስፈልገው ህንጸት አንጻር ቁሳዊ ድጋፍ የመሰብሰብ ጥረት ዳግም ጉልበት እንዲኖረው አብረው እየሰሩ ነው:: ይህም የተልዕኮ ቅንነት፣ ግንዛቤ እና ኃላፊነት ዳግም የመላው ቅዱስና ጽኑ የእግዚአብሔር ህዝብ የዘወትር ኑሮ አካል እንዲሆን በማለም ነው» (በርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ፍራንቼስኮስ ለጳጳሳዊ ልዑካን ማኅበራት ብሔራዊ አመራሮች የተላለፈ መልእክት፣ እ.ኢ.አ በሰኔ 1 ቀን 2018 ዓ.ም.):: «አራቱ ማኅበራት፣ ማለትም ጳጳሳዊ የወንጌል ስርጭት ልዑካን ማኅበር (Pontifical Society for the Propagation of the Faith)፣ ጳጳሳዊ የሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ማኅበር (Pontifical Society of St. Peter the Apostle)፣ ጳጳሳዊ የቅዱሳን ሕጻናት ማኅበር (Pontifical Society of the Holy Childhood)፣ እና ጳጳሳዊ የልዑካን ኅብረት (Pontifical Missionary Union) ሁላቸውም አንድ የጋር የሆነ ዓላማ አላቸው:: ይሄውም በእግዚአብሔር ህዝብ ዘንድ ዓለም አቀፍ የተልዕኮ መንፈስ እንዲጎለብት ማስቻል ነው (የመድኃኔዓለም ተልዕኮ - Redemptoris Missio 84)::»